የሰ/መ/ቁ. 66945

ሰኔ 2 ቀን 2003 ዓ.ም

ዳኞች፡- ተገኔ ጌታነህ

ሐጎስ ወልዱ

አልማው ወሌ

ነጋ ዱፍሣ

አዳነ ንጉሴ

**አመልካች** ፡- የእንግሊዝ ህጻናት አድን ድርጅት - ጠበቃ ጥላዬ ተገኝ - ቀረቡ

**ተጠሪ** ፡- አቶ ገአስ ኡስማን - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

በዚህ መዝገብ የተያዘው ክርክር በአሰሪና ሰራተኛ ጉዳይ ወሣኝ ቦርድ የተጀመረ ነው፡፡ ጉዳዩ አሰሪ የሆነው የአሁን አመልካች ሰራተኛ በሆኑት በአሁን ተጠሪ ላይ የወሰደውን የስንብት እርምጃ የሚመለከት ነው፡፡ ተጠሪ በአመልካች ድርጅት የተወሰደብኝ እርምጃ ህገ ወጥ በመሆኑ የተቋረጠብኝ ክፍያ ተሰጥቶኝ ወደ ስራዬ እንድመለስ ይወሰንልኝ ሲሉ በአመልካች ላይ ክስ መስርተዋል፡፡ አመልካች ጉዳዩ በሌሉበት እንዲታይ ተደርጐ በውሣኔው ላይ ቢገለጽም ተወካዮቹ ቀርበው በጽሁፍ መልስ የሰጡ ስለመሆኑ ግን የክርክሩ ሂደት ያሣያል፡፡ የአመልካች የመከላከያ መልስ ክርክርም የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የስንብቱን ተገቢነት ይገልጻል የሚለውን መልስ አቅርቦ የተከራከረ መሆኑን የክርክሩ ሂደት ያሣያል፡፡ ክሱ የቀረበለት የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ዞን አራት ከፍተኛ ፍርድ ቤትም ጉዳዩ በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣኑ መታየቱ ፍርድ ቤቱ ክሱን አዛውሮ ከማየት ስልጣኑ አንጻር ተገቢ ነው የሚለውን ምክንያት በመስጠት በስልጣን ረገድ የተነሣውን የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ ከአለፈው በሁዋላ ዋናውን ጉዳይ በተመለከተም መርምሮ ስንብቱ ህገ ወጥ ነው ወደሚለው ድምዳሜ ደርሶ አመልካች ድርጅት ተጠሪን አሰናበተ ከተባለበት ከጥቅምት ወር 2001 ዓ.ም እስከ ጥር 26 ቀን 2002 ዓ.ም እንዲሁም ከጥር 27 ቀን 2002 እስከ የካቲት 29 ቀን 2003 ዓ.ም ድረስ ያለውን ውዝፍ ደመወዝ ከቆላ አበሉ ጋር የደመወዝ ጭማሪ እንዲሁም ሌሎች ጥቅማጥቅሞችን በመክፈል ወደ ቀድሞው የስራ መደብ እንዲመልሰው በማለት ወስኗል፡፡ ጉዳዩ በይግባኝ የቀረበለት የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ጉዳዩን በይግባኝ የመመልከት ስልጣን የሌለው መሆኑን ጠቅሶ መዝገቡን ዘግቶታል፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበውም ይህንኑ ውሣኔ በመቃወም ለማስለወጥ ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ መሰረታዊ ይዘቱም ጉዳዩ በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣኑ የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት መመልከቱም ሆነ ጉዳዩን የመራበት ስርዓት የፍታብሔር ሥነ ሥርዓት ህጉን የተከተለ ባለመሆኑ ሊታረም የሚገባው ነው በማለት መከራከራቸውን የሚያሣይ ነው፡፡ አቤቱታው

ተመርምሮ በሰበር ችሎቱ ሊታይ የሚገባው መሆኑ ታምኖበት ለተጠሪ ጥሪ ተደርጐላቸው ቀርበው የጽሁፍ መልስ የሰጡ ሲሆን በመልሣቸው ላይም የቀረበው አቤቱታ ተቀባይነት ሊያገኝ አይገባም በማለት ተከራክረዋል፡፡

ይህም ችሎት በቅድሚያ ምላሽ ሊሰጠው የሚገባው አቢይ የህግ ነጥብ ላይ ብቻ በማተኮር መዝገቡን መርምሯል፡፡ በዋነኛነት ሊፈታ የሚገባው የነገሩ ጭብጥ፡-

የአሰሪና ሰራተኛን ጉዳይ አዋጅ ቁጥር 377/96 "ን" መሠረት አድርጐ የሚነሣውን የግል የስራ ክርክር በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣኑ በማየት የመዳኘት ስልጣን የማነው? የክልሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ነው? ወይስ የክልሉ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት? የሚለው መሆኑን ተገንዝቧል፡፡ ለተያዘው ጭብጥ ምላሽ የማግኘቱ ጉዳይ ስለ ስራ ክርክር ስለ ቦርድና ስለ ፍርድ ቤት ስልጣን የሚገልጹትን የአዋጅ ቁ. 377/96 ድንጋጌዎችን ተመስርቶ ጭብጡን መመርመርን ይጠይቃል፡፡ አዋጅ ቁጥር 377/96 ከአዋጅ ቁ. 25/1988 በኋላ የወጣ ሲሆን በአንቀጽ 136/3/ ስለ ስራ ክርክር ምንነት ትርጓሜ የሚሰጥ ድንጋጌ ከመያዙም በላይ የዚሁ አዋጅ አንቀጽ 147 ስለቦርድ ስልጣን የሚደነግገው ሲሆን የፍ/ቤት ስልጣንን ደግሞ የሚደነግገው የአዋጁ አንቀጽ 138/2/ ነው፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 138/1/ የተዘረዘሩትንና መሰል የግል የስራ ክርክሮችን የመዳኘት ስልጣን ለፍ/ቤት መስጠቱን ከዚህ ድንጋጌ መረዳት ይቻላል፡፡ አዋጁ የስራ ክርክርን የክልልና የፌዴራል ጉዳይ ነው የሚል መለኪያ በመስጠት የስነ-ነገር የዳኝነት ስልጣን መከፋፈሉን በግልጽ አያሣይም፡፡ በአዋጅ ቁጥር 322/95 "ም" ሆነ በህገ መንግስቱ መሠረት የክልሉ ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ስራ ክርክርን አስመልክቶ የፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ስልጣንን በውክልና ሊመለከት ይችላል የሚባልበት አግባብም የለም፡፡ በአዋጁ አንቀጽ 138/1/ ድንጋጌ መሠረት ለፍ/ቤት የሰጡትን የስራ ክርክሮችን በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣን የማየት የስረ ነገር ስልጣን የክልሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት መሆኑ በግልጽ ተቀምጧል፡፡ የአዋጁ አንቀጽ 139/1/ /ሀ/ ደግሞ በክልሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በስራ ክርክር ችሎት የተሰጡ ውሣኔዎች ላይ የክልሉ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የስራ ክርክር ችሎት የይግባኝ ስልጣን እንዳለው ያሣያል፡ በመሆኑም የክልሉ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የስራ ክርክር ችሎት በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 138 መሠረት በክልሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሚታዩት ጉዳዮች ላይ የይግባኝ ስልጣን ያለው መሆኑን የአዋጁ አንቀጽ 139/1/ሀ/ በግልጽ ያሣያል፡፡

ወደተያዘው ጉዳይ ስንመለስ የተጠሪ የዳኝነት ጥያቄ የስራ ውል ከህግ ውጭ የተቋረጠ ስለሆነ ውዝፍ ደመወዝ ተከፍሎ ወደ ቀድሞው ስራ እንዲመለስ ፣ ጭማሪ ደመወዝ እንዲከፈለኝ ፣ የቆላ አበል እና ሌሎች ጥቅማጥቅሞች እንዲከፈሉኝ ይወሰንልኝ የሚል ሲሆን በይዘቱ በአዋጅ አንቀጽ 138/1/ለ/ መሠረት የሚታይ የግል የስራ ክርክር ሁኖ በጉዳዩ ላይ በሚሰጠው ውሣኔ ቅሬታ ያለው ወገን ይግባኙን ለክልሉ ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የስራ ክርክር ችሎት በአንቀጽ 139/1ሀ/ መሠረት አቅርቦ የሚያሣይበት ጉዳይ ነው፡፡ የአፋር ክልል ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣኑ ሊመለከት የቻለው ጉዳዩን ለማየት ስልጣኑ በህጉ በግልጽ ተሰጥቶኛል በሚል ምክንያት ሣይሆን የክስ መዛወር ጥያቄ ሲቀርብ ለማስተናገድ የምችለው እኔ ነኝ በሚል ምክንያት ስለመሆኑ ከክርክሩ ሂደት መገንዘብ ችለናል፡፡ ይሁን እንጂ የክስ ይዛወርልኝ ጥያቄ /Change of Venue/ የሚስተናገድበትን አግባብ ህጉ የዘረጋው ስርዓት ያለ ሲሆን የስር የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ለብይኑ ዋቢ ያደረገው በ1958ቱ የፍትሐብሔር ስነ ሥርዓት ህጉ አንቀጽ 31 ስር የተመለከተው አንዱ ሲሆን ከዚህ ህግ በሁዋላ በፌዴራልም ሆነ በክልሎች የወጡት የፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጆችም ተመሣሣይ ይዘት ያለውን ድንጋጌ ስራ ላይ አውለው ይገኛሉ፡፡ አንድ ክስ ወደ ሌላ ስፍራ ሊዛወር

የሚችልበትን አግባብ ከሚደነግጉት የስነ ስርዓት ህግ ድንጋጌዎች ይዘትና መንፈስ መገንዘብ የሚቻለው ደግሞ ጥያቄው ከተከራካሪ ወገኖች የሚቀርብ መሆኑና ህጋዊ ምክንያቶች ተብለው በህጉ ከተመለከቱት ሁኔታዎች ውስጥ አንዱ መሟላት ያለበት መሆኑን ነው፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግን የአፋር ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ወደራሱ ያዞረው በተከራካሪ ወገኖች የክስ ይዛወርልኝ አቤቱታ ቀርቦለትና በህጉ ስር የተመለከቱት ቅድመ ሁኔታዎችም ተሟልተው ስለመሆኑ የክርክሩ ሂደት የማያሣይ መሆኑን ተገንዝበናል፡፡ በመሆኑም የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ወደ ራሱ አዙሮ የተመለከተው ህጋዊ ስርዓቱን ተከትሎ አይደለም ፣ በውጤቱም በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣኑ እንዲመለከተው በህጉ ያልተሰጠውን ስልጣን በመውሰድ ጉዳዩን በማየት በህጉ ጥበቃ ያገኘነው የተከራካሪ ወገኖች የይግባኝ መብት ያጣበበ ሁኖ ተገኝቷል፡፡ በዚህም ምክንያት በጉዳዩ ላይ የተሰጠው ውሣኔ መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት ያለበት ሁኖ ስለተገኘ ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሣ ኔ

1. በአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ዞን አራት ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁጥር 00126 የካቲት 29 ቀን 2003 ዓ.ም የሰጠው ውሣኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁጥር 348/1/ መሠረት ተሽሯል፡፡
2. ጉዳዩ በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣን ሊታይ የሚገባው በክልሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ሲሆን በዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣኑ ሊታይ የሚችልበት ህጋዊ ምክንያት/አግባብ የለም ብለናል፡፡
3. በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር የወጣውን ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ የራሣቸውን ይቻሉ ብልናል፡፡

   መዝገቡ ተዘግቷል፤ ወደመዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

እ.ከ